Arlington Public Schools

የካቲት 6, 2023

ውድ የ APS ቤተሰቦች፣

Arlington Public Schools (APS) (የአርሊንግተን ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች) ለ 2023-24 የትምህርት ዘመን ዝግጅት በማድረግ ላይ የ አምስተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን የመኖሪያ አድራሻን ለማረጋገጥ Home Address Confirmation Process (HACP) (የመኖሪያ ቤት አድራሻ ማረጋገጫ ሂደት)ን አስጀምሯል። ይህም ትክክለኛ የሆኑ የተማሪዎች መዝገቦችን እንድንይዝ እና የ ቨርጂንያ ህግን እና የ የቅበላ ፖሊሲያችንን ለማክበር የሚያስችለን ይሆናል።

ባለፉት ግዜያት፣ እንደአስፈላጊነቱ የመኖሪያ ቤት አድራሻ የማረጋገጥ ስራዎችን አካሂደናል፣ ነገር ግን ይህ ሂደት ዋና በሚባሉ የትምህርት ሽግግር ግዜያት ላይ በሁሉም ተማሪዎች ላይ ቀጣይነት ያላቸው የመኖሪያ ቤት አድራሻ የማረጋገጥ ስራዎችን እንድንሰራ የሚያስችለን ይሆናል።

በዚህም፣ አሁን ላይ የአምስተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች በምዝገባ ግዜ ገቢ ያቀረቧቸውን የመኖሪያ ቤት አድራሻ የያዙ ሰነዶችን እንዲያድሱ ወይም መልሰው እንዲያቀርቡ እየጠየቅን እንገኛለን። **እነዚህን ለማቅረብ የመጨረሻው ቀን መጋቢት 15, 2023 ነው።**

ይህ አዲስ ሂደት APS የሚከተሉትን ነገሮች እንዲያደርግ ያስችለዋል፡

- የእያንዳንዱ ሰነድ ላይ ያለ ተማሪ ትክክለኛ መዘገብ እንዳለን ማረጋገጥ፡
- የተወሳሰቡ የኑሮ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን በመለየት ሰራተኞቻችን እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ቁሶችን እና ድጋፎችን መስጠት እንዲችሉ ማድረግ፡
- ይህ የሚካሄደው ተማሪዎች ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለመሸጋገር በሚዘጋጁበት ግዜ ነው፡
- ተማሪዎች በአርሊንግተን ውስጥ መኖራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ፍትሃዊ እና ወጥነት ያለው ሂደት እንዲኖር ያደርጋል ፣ ከዚህም በተጨማሪ
- በቨርጂኒያ ኮድ § 22.1-3 እና በ APS የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ J-5.3.30 ቅበላዎች መሰረት ተማሪዎቻችንን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል በሚያስችል መልኩ ሀብቶቻችንን በተቻለ መጠን በብቃት እያስተዳደርን እና እየመደብን መሆናችንን ያረጋግጣል፡

አንዴ ሁሉም ሰነዶች ወደ ትምህርት ቤትዎ ገቢ ከተደረጉ በኋላ፣ ሰነዶችዎ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ እና የመኖሪያ አድራሻዎን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ለማረጋገጥ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ከእርስዎ ጋር ክትትል እናደርጋለን። እንዲሁም መረጃዎ መቼ እንደታደሰ በParentVUE ውስጥ በመግባት ማረጋገጥ ይችላሉ።

እስከ መጋቢት 15፣ 2023 ድረስ ሰነዶቹ ገቢ ካልተደረጉ፣ ወይም ድጋፍ የሚያስፈልግባቸው ውስብስብ ነገሮች ያሉ ከሆነ፣ እነዚያን ቤተሰቦች በማገዝ ችግሮችን በመፍታት ላይ ድጋፍ እናደርጋለን። የቤት አድራሻዎን እስከ ግንቦት 15፣ 2023 ድረስ ማረጋገጥ ካልቻልን፣ ተማሪዎን እና ሁሉም ወንድም እና እህቶቹ/ቿ ለ2023-24 የትምህርት ዘመን ከምዝገባ ውጪ እንዲሆኑ በማድረግ እርስዎ አሁን በሚኖሩበት የትምህርት ቤት ስርዓት እንዲያስመዘግቧቸው የሚያግዝዎትን ግብአት እናቀርባለን።

ተማሪዎች አሁን ላይ ባለው የትምህርት ዘመን ከምዝገባ ውጪ እንዲሆኑ አይደረግም- ይህ የሚመለከተው ለ 2023-24 የትምህርት ዘመን ብቻ ነው። ቀደም ሲል ከምዝገባ ውጪ እንዲሆኑ የተደረጉ ልጆች ቤተሰቦች፣ ተመልሰው አርሊንገተን ውስጥ መኖር ጀምረው ከሆነ፣ በ APS ውስጥ መልሰው ማስመዝገብ ይችላሉ።

የሚያስፈልጉ ሰነዶች እና እንዴት ገቢ ማድረግ እንደሚቻል የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ካስፈለግዎ ይህ ደብዳቤ መልሰው ለማጣቀስ ይጠቀሙበት። ተጨማሪ ድጋፍ ካስፈለግዎ፣ እባክዎን የተማሪዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ ወይም የ HACP ድህረ-ገጽን www.apsva.us/HACP ላይ በመሄድ ይጎብኙ።

ለሚሰጡት ድጋፍ እና ትብብር እናመሰግናለን!

ከ ሰላምታ ጋር፣

Darrell Sampson, Ed.D., MA, LPC, NCC
ዋና ዳይሬክተር፣ የተማሪዎች አገልግሎት

Arlington Public Schools

# <u>የመኖሪያ ቤት አድራሻ ማረጋገጫ ሰነዶች</u>

APS መጀመሪያ በምዝገባ ግዜ የጠይቅናቸውን ሰነዶች እንዲቀርቡለት ይጠይቃል። ተማሪዎች የተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት ዜግነት የሚያረጋግጡ፣ የማሕበራዊ ደህንነት መረጃ የያዙ ወይም ማናቸውም ከዜግነት ጋር የሚዛመዱ ሰንዶችን አይጠይቁም። ይህ ሂደት በ APS ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች አሁን ላይ አርሊንገተን ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ባቻ የሚያገለግል ሆኖ፣ APS የተቀበላቸውን ማናቸውንም መረጃዎች ለሌሎች ተቋማት፣ የኪራይ ኩባንያዎች፣ የመንግስት አካላት ወይም ለቤቶች ባለስልጣናት አስልፎ አይሰጥም።

## የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት

- የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም የመተማመኛ ሰነድ
- የውሳኔ ሰነዶች (ለአዲስ ቤት ግዢ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነዱ ገና ያልተመዘገበ ከሆነ)
- የይዞታ ሰነድ ስለመጠየቅ የተመለከተ መረጃ በአርሊንግተን ካውንቲ የመሬት መዛግብት ክፍል ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል።

## የመኖሪያ ቤት መከራየት

- አሁናዊ የሊዝ ውል ከህንፃው ባለቤት ጋር (በሁለቱም በተከራይ እና በንብረቱ ባለቤት የተፈረመበት መሆን አለበት)

## አማራጭ የኑሮ ሁኔታዎች – ህጋዊ የመኖሪያ ማረጋገጫ

- **ቅጽ A** – በአርሊንገተን ነዋሪነትን የሚያረጋግጥ ነው (አርሊንግተን ውስጥ ኗሪ በሆነ ወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ)
- **ቅጽ B** – አሁናዊ የኪራይ/ሊዝ ውል (በይፋዊ ኪራዩ ላይ የተጠቀሰ ሰው የተሞላ)

## አጋዥ ሰነዶች - አሁን ላይ ያሉበትን አድራሻ ለማረጋገጥ ከሚከተሉት ውስጥ ሁለቱን ማቅረብ አለብዎ

- የፌደራል፡ የግዛት ወይም የንብረት ታክስ ተመላሽ፡ የተሽከርካሪ ምዝገባ፡ አሁን ስራ ላይ ያለ እና አሁናዊ የሆነ አድራሻ ያለበት የ VA የአሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ፡ አሁናዊ የደሞዝ መክፈያ ዝርዝር ወይም የእግድ ሰነድ፡ አሁናዊ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ/ቢል፡ ወይም ከ አርሊንገተን ካውንቲ የተሰጡ የገንዘባዊ ድጋፍ ሰነዶች።

ተጨማሪ መረጃ በነዋሪነት አድራሻ ማረጋገጫ ድህረ-ገጽ www.apsva.us/HACPላይ ይገኛል።

## <u>ሰነዶችን ገቢ ማድረግ</u>

ቤተሰቦች ሰነዶችን ከሚከተሉት ሁለት መንገዶች በአንዱ ማስገባት ይችላሉ፡

- **ኦንላይን ገቢ ማድረግያ**: ለግላዊነት እና ለመረጃ ደህንነት ሲባል ቤተሰቦች ደህንነቱ የተጠበቀ ገቢ ማድረግያ ድህረ-ገጽ ብቻ መጠቀም አለባቸው እና ሰነዶችንም በኢሜል መላክ የለባቸውም። ቤተሰቦች ሰነዶቻቸው እንደደረሱ እና በስርዓቱ ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ሬጅስትራር ኢሜይል ይደርሳቸዋል። ሰነዶች በአስተማማኝ በሆነው የገቢ ማድረግያ ድህረ-ገጽwww.apsva.us/HACPበመጠቀም ገቢ መደረግ አለባቸው።

Arlington Public Schools

- **በአካል፡** ቤተሰቦች በተማሪያቸው ትምህርት ቤት በአካል በመቅረብ ወይም Syphax Education Center (2110 Washington Blvd.) ላይ ወደሚገኘው APS Welcome Center (የእንግዶች መቀበያ ማዕከል) በመገኘት ስነዶቻቸውን ገቢ ማድረግ ይችላሉ

**የተወሳሰቡ የኑሮ ሁኔታዎች**

የተወሳሰበ የኑሮ ሁኔታ ምሳሌ የሚሆኑት የመኖሪያ ቤት የሌላቸው ቤተሰቦች ወይም ቤት አልባነት እያጋጠማቸው የሚገኙ ቤተሰቦች ናቸው። ይህም ባላቸው የቋሚነት ሁኔታ እና የኑሮ ሁኔታቸው አመቺነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ፣ ይህም በሆቴል ውስጥ መኖር፣ ከመኖሪያ ቤት ወደ መኖሪያ ቤት መንቀሳቀስ ወይም ከ ዘመዶች እና ጓደኞች ጋር አብሮ መኖርን የሚያጠቃልል ነው። የመኖሪያ ቤት የሌላቸው ተብለው የተለዩ ቤተሰቦች በ federal McKinney-Vento Homeless Assistance Act መሰረት ከለላ ይደረግላቸዋል።

ሌሎች ተጨማሪ የተወሳሰቡ የኑሮ ሁኔታዎች ተብለው ሊመደቡ የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ እነዚህም በሰራተኛው መረጋገጥ አለባቸው። ቤተሰቦች ድጋፍ ወይም ተጨማሪ መረጃ ሲፈልጉ የተማሪዎን ትምህርት ቤት ወይም የ APS Welcome Center እንዲያነጋግሩ እናበረታታለን።

**የእውቂያ መረጃ**

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ጥያቄዎች፣ እባክዎን የተማሪዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ ወይም በ ይጎብኙwww.apsva.us/HACPላይ ያለውን የ Home Address Confirmation (ቤት አድራሻ ማረጋገጫ) ድህረ-ገጽ ይጎብኙ። ከዚህም በተጨማሪ ወላጆች ድጋፍ ሲያስፈልጋቸው የ APS Welcome Center ጋር በመሄድ ያማክሩ ወይም 703-228-8000 ተጠቅመው ይደውሉ (ኣማራጭ 3 ን ይምረጡ) ወይም registration@apsva.usይጠቀሙ።